# ምላሽ ለአቶ ዳንኤል ክብረት

<<ሸዋ የጥንትና ዛሬ መገናኛ>> በተባለ ርዕስ ያቀረብከውን ፍጹም ቱሪ ማንቱሪ፤ በሸዋ ሕዝብ ኪሣራ ለውሸት የማስመሰል ኢትዮጵያዊነት ለማራገብ አቅደህ፤ ይልቁንም ያለሙያህና ችሎታህ የመካለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክን ሆንብለህ በስፍራና በጊዜ ፈጽሞ የማይገናኙ ሁነቶችን አሳስተህ በማቅረብ አስቀድሞ በባሕር ማዶና አገር በቀል የፀረ ኢትዮጵያ ቅጥረኛ ስብስቦች ማለትም እነ ኦነግ፤ ሕወሐት፤ ሻዕቢያ ሲነዙ የነበረውን፤ ዛሬ ደግሞ የወቅቱ አስመሳይ የኢትዮጵያዊነት ጨንበል አጥልቀው የሚያወናብዱትን የፖለቲካ ነጋዴዎችን ለመደለል አስበህና አቅደህ የፃፍከውን የፈጠራ ትርክት እኛ የሸዋ ሕዝብ ድርጅት በአጽንኦት የምንቃቀም መሆኑን ቅጥሎ በዝርዝር እንገልጻለን።

**፩ኛ.** "ከትግራይና ከቤተ ዐምሐራ የመጡት በብዛት ክርስቲያን የነበሩት ሕዝቦች..." በማለት የጻፍከው ፍጹም ውሸት ነው። ከሁሉ በተቀዳሚ ትግሬ የተባላ አገርና ሕዝብ በታሪክ ሰነድ የተፈጠረው ከሰባተኛው ዓ.ም በአረቢያ ባሕረ ሰላጤ ምድር የእስልምና ሃይማኖት ተነስቶ በመስፋፋቱ ምክንያት የአክሱም የኢትዮጵያ አጤ መንግሥት በገባሮቹ በተለይም በቤጃዎች ተወሮ በመውደቁ ምክንያት ነው።

ከስምንተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የቤጃ ልዩ ልዩ ጎሣዎች በጥንቱ ያክሱም ግዛት ከመረብ ወንዝ በስተሰሜንና በስተደቡብ ስፍረዋል። ቤጃኛ ቋንቋቸውን ከግእዝና ከሕባባ ወይም ትግረ ተናጋሪው ነባር ሕዝብ ጋራ አቀላቅለው፤ በክርስትና ሃይማኖትንም አምነው <u>ትግሬ</u> ተብለዋል።

የጥንታዊት ኢትዮጵያ አክሱም ንጉሠ ነገሥት ግዛት በቤጃዎች ሲወረር አክሱማውያን ነገሥታቱና መኳንንቱ መዲናቸውን ለቀው ወደ ደቡብ ዐማራውና አገው አገር ሸሽተዋል። ይህም ሂደት በሚገባ ተመዝግቧል። በዚህም መሠረት አጤ ድል ነአድ ከአክሱም ሲባረር ወደ ሸዋ ዐማሮች ዘንድ መንዝና መርሃ ቤቴ መጥቶ ቆይቷል።

ከሁሉ በተቀዳሚ ግን ምድረ ሸዋ በአፍሪቃ አባይ ሸለቆ ከቅድመ ፈርኦናዊ ሥርዎ መንግሥት ምሥረታ አስቀድሞ የኖረ፤ በጥንት ግብፃውያን ፑንት የአበሻ የአማልክትና የቅመማቅመም አገር ጠነጠር ማለትም የእግዚአብሔር አገር (God's lanfd) የተባለው ክፍል እንደነበረ እጅግ በጣም ሰፊ የሂሮግሊፊክስ የታሪክ ሰንድ ያረጋግጣል። በሸዋ ምድር ከሰሜን እስከ ደቡብ ማለትም በመንዝና ይፋት ኤፍራታ የመሸራ ድንጋይ ቁም ድንጋይ ብዙ ሐውልቶች፤ በደቡብ ሸዋ በጉራጌ ጥያ እስከ ቱርካና ሐይቅ ደርስ የሚገኙት እጅግ በጣም ብዙ ትክል ድንጋይ ሐውልቶች ቋሚ ምስክር ናቸው። በአክሱም ጥንታዊት መዲና ዙሪያ የቆሙት ሕውልቶችም የዚሁ ተከታዩች ለመሆናቸውና ከዘመነ ፈርኦን ሥርዎ መንግሥት ጀምሮ የተሠሩ መሆናቸው ቢታወቅም እንኳ የምዕራቡ ዘረኞች ሆንብለው እድሜያቸእውን ቀንሰው በዘመነ ክርስትና እንደተሠሩ ተደርጎ በነ አኖ ሊትማ፤ንና ኮንቲ ሮሲኒ የተናፈሰው ከፀረ ኢትዮጵያ ሴራው አንዱ ነው።

የሸዋ ግዛት በስተምሥራቅ የኤዴን ባሕረ ሰለጤና ሕንድ ውቅያኖስ ጠርፍ በመለስ ሲሆን በምዕራብም ያባይ ወንዝ ሸለቆ ያዋስነዋል። ጥንታዊው ነባር ሕዝቡም ዐማራ፣ ጉራጌ፣ ጋፋት፤ ጎንጋ፤ አገው፣ ከምባታ ናቸው። በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ምድር ከ2743 ዓ.ዓ ጀምሮ ከፍተኛ ሥልጣኔ እንደነበረና ከጥንት ግብፅ ፈርኦናዊ መንግስሥት ከ፩ኛው ከሱሁሪን ጀምሮ እስከ ፲፰ኛው የእነ ንግሥት ሐትሼፐሱት (1504-1482) እንዲሁም ከ፲፱ኛው እስከ 1100 ዓ.ዓ ከፑንት የአበሻ ሕዝብ ጋራ የሁለትዮሽ ንግድ፤ ሃይማኖት፤ ባሕልና ቋንቋ ዝምድና ነበራቸው። ስለዚህም ነው የአበሻ ሕዝብ ከአረብ ባሕረ ሰላጤ ምድር ፈልሶ በአፍሪቃ አባይ ሸለቆና አምባ የላቀ ሥልጣኔና "ሴማዊ" ቋንቋ አመጣ ተብሎ በአውሮፓ ዘረኞች ቅኝገዥ ተስፋፊዎችና በመጤ ሃይማኖት ተጽእኖ የተመለመሉት አገር በቀል ቅጥረኞች ሲለፈፍ የቆየውንና ያለውን ተረት ተረት አሽቀንጥረን የጣልነው። ይልቅስ በተቀራኒው የአበሻ ጥቁር ሕዝብና ዘርያ ቀይ ባሕርን ተሻግሮ፤ በአረቢያ ሰርፀ ምድር፣ በመሶጵታሚያ እስከ ሕንድ ንዑስ አህጉር፤ ፖሊኔሽያ፤ አውስትራሊያ፤ ታስማኒያ ድረስ ተሰራጭቶ የሚገኝ የጥቁር ሕዝብ ዘር ወገን መሆኑን በአጽንኦት እናሰምርበታለን። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከአንድ የጥቁር ሕዝብ ዘር ወገን ነው። ነገር ግን በሃይማኖትና በቋንቋ ሽፋን ሴማዊና ካማዊ ወይም ኩሻዊ ብሎ መከፋፈል ያውሮፓ የነጭ ዘርኞችና ቅኝ ገዥ ተስፋፊዎች ዋና ሴራና ተንኮል ነው እንጂ ሥነ ፍጥረታዊ መሠረት የለውም:::: በአፍሪቃ አባይ ሸለቆ ምድር የኢትዮጵያንና የጥንት ግብፅን የጥቁር ሕዝብ ሥልጣኔ ቅርስና ፍራሻ ያውሮፓ ነጭ ዘርያ ተብዬዎች ፈጠራ ለማስመስል ታቅዶ የተቀነባበረ የፈጠራ ተረት ተረት በያይነቱ ይገኛል።

ጥንታዊ የግእዝ ቋንቋ በመሶጵታሚያና ባቢሎን ከነበረው ከለዳዊ ቋንቋ ጋራ በቀጥታ ይዛመዳል። ግእዝ ማለትም አንደኛ ማላት ነው። ከዕብራይስጥ፤ ከሱርሱርትና ከአረብ ይቀድማል። ያማርኛ ቋንቋም በቀጥታ ከከለዳዊው ጥንታዊ ቋንቋ ጋራ ይዛመዳል። ከለዳዊው በአረፍተ ነገር ግንባታ ሥርዓቱ ልክ እንድ ዐማርኛ ግሱ በስተመጨረሻ ላይ ይገባል። ይህ ዓይነቱ የአገባብ ሥርዓት በፋርስኛ፤ በሕንድኛ፤ በአገውኛ፤ በጋልኛ፤ በአፋርኛ፤ ወዘተረፈ ቋንቋዎች ሁሉ ይታያል። የምዕራብ አውሮፓ ዘረኞች ግን የሕንድንና የፋርስን ወዘተረፈ ቋንቋዎች ኢንዶ ዩሮፒያን ብለው ይቀላምዳሉ። የኢትዮጵያ ሴማዊ ቋንቋ ተብዬዎች ያማርኛ፤ የትግሪኛ፤ የጉራጌኛ ወዘተረፈ ግሥ በስተመጨረሻ መሆን ከካማዊ ቋንቋ ቤተሰብ ከተባሉት ማለትም ከአገውኛ፤ ከወላምኛ፤ ከጋሊኛ፤ ከሱማሌኛ፤ ከአፋርኛ፤ ከቤጃኛ የተገኘ ተጽዕኖ ብለው እንበለ እፍረት ዐይናቸውን በጨው አጥበው ወሻክተዋል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ያማርኛ ቋንቋን ጥንታዊነት ክድዋል። የግእዝ የቅርብ እኅት መሆኑን ደብቀዋል። ይልቁንም ከጥንታዊው የግብፅ ቋንቋ ጋራ ያለውን ቀጥተኛ ዝምድና ሸፍጠዋል። ያማርኛ ቋንቋን የቅርብ ዘመን ዝንቅ (Pidgin) ቋንቋ፣ ከአክሱም መንግሥት ውድቀት ወዲህ በዘመነ ዛጉዌ ዘመነ መንግሥት የተፈጠረ እንደሆነ አስመስለው አንዳንድ ይሁዲ ሴማዊ ተብዬ ያሜሪካና አውሮፓ መጤቃዎች በኢትዮጵያዊ ዐማራ ሕዝብ ጥላቻና ነፃ ሕዝብነ ትሳቢያ

ከፍተኛ ቅናትና ምቀኝነት የተጠናወታቸው እንደ ቤንድር፤ ኽትዝሮን ወለፍ ለስላው፤ ሚትቮኽ፤ ኡሉንዱርፍ ወዘተረፈ. እንዲሁም አብዛኛው አገር በቀል የአስኮላው ትምህርት ቤት ምልምሎችና አሽቃባጮች እነ ኃይሉ ፉላስ፤ ባዬ፤ በላይ፤ አላምረው ግርማ፤ አበበ ወዘተረፈ የመሳሰሉት የሰሙትን ዝባዝንኪ አስተጋብተዋል።

**፪ኛ.** አቶ ዳንኤል ስትወሻክት የሸዋን ስምና የይፋትን አጠራር ከጋሊኛ ኢፋት ማለትም ብርሃን ማለት ጋራ ለማስማማት ሞክረሃል። ነገር ግን ባማርኛ ቋንቋ ይፋት የሚለው መጠሪያ ገሃድ፣ ግልጽ፣ ይፋ ያልተደበቀ፣ ያልተሰወረ ምስጢር ያልሆነ መሆን ማለት ሲሆን ይህም ለምን እንደሆነ ትክክለኛውን መልስ እንሰጣለን።
በኢትዮጵያ የአጤ መንግሥት ግዛት ሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃ ውስጥ የአስልምና ሃይማኖት ከአረቢያ ቀይ ባሕርን ተሻግሮ የተስፋፋው በአረብ ነጋዴዎችና ባሃይማኖት ሰባኪ መጤ ስፋሪዎች አማካይነት ነው እንጂ በጅሃድ የሃይማኖት ጦርነት ወረራና መስፋፋት አይደለም። ስለሆነም ከስምንተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የእስልምና ሃይማኖት ከምሥራቅ ከኤደን ባሕረ ሰላጤ እስከ ምዕራብ ግቤ ወንዝ ድረስ ተሰራጭቷል። በተቀዳሚ ጥንታዊው የሸዋ ሱልጣናት (896 - 1285) ቀጥሎም የይፋት አዳል ወላስማ ሥርዎ መንግስት (1285 - 1577) ገባሪዎቹ ንዑስ የደዋሮ፣ የሃድያ፣ የአራባቢኒ፣ የሻርካ፤ የባሌ፤ የአዳል፣ የፈጠጋር፣ የሁባት፤ የጅዳ ወዘተረፈ እስላማዊ ያካባቢ ሱልጣናት እንደነበሩ የተረጋገጠ ሐቅ ነው።
የሸዋ፤ የይፋት፣ የፈጠጋራ፤ የደዋሮ፣ የወጂ፣ የባሌ፤ የሃርላ ወዘተረፈ ነባር ያማራ ሕዝብ ከፊሉ እስልምናን የተቀበለው ወገን በጥቅል አርጎባ ተብሎ ይጠራል። አርጎባ ማለትም አረብ ገባ፤ እስላምነት ተሰበከ ማለት ነው። በሸዋ ሡልጣናት የማኽዙሚ፣ በይፋት አዳል የዑመር ወላስማ ሥርዎ መንግሥት እስልምናን በመላው ኢትዮጵያ ለማስፋፋት ዘወተር ጦርነት ከአጼው መንግሥት ጋራ ሲያደርጉ ቆይተዋል። እስላም ዐማሮች ዐርጎቦች፤ አዳሎች ይባላሉ።
የአርጎባ አዳል ወላስማ ሱልጣናት በ፲፮ው ክፍለ ዘመን ከሸዋ ይፋት ወደ ሐረርጌ ሐረር ስለተዛወረና ያርጎባ ምደር ከግራኝ አሕመድና ከተከታዩ የጋላ ወረራ በኋላ በደንከል (አፋር)፤ ኢሳና ጋላ ዘላኖች በቅርብ ዘመን ከ17ኛው ምዕተ ዓመት ወዲህ መያዙ ምክንያት አዳልን ከአፋር ጎሣ ጋራ ያለአግባብ በማያያዝ የአርጎባ አዳል ሕዝብን አሳስተው ተርከዋል። በዘመነ ደርግ አፋሮች አዳል ተብለን መጠራታችን ስሕተት ነው ሰማችን አፋር ነው ብለው አውጀዋል። ልክ ዛሬ ራሳቸውን በራሳቸው ኦሮሞ ብለው የሚጠሩትና የኦሮሞ ብሔረተኛነትን በፈጠራ ተረት ፈልስመው፤ ልዩ ልዩ የጋላ ጎሣዎች ጋላ መባል የለብንም ኦሮሞ ተብለን እንጠራ፤ ኦሮሚያ የሚባል አገር እንፍጠር ብለው እነ ኃይሌ ፊዳና ብጤዎቹ አስቀድሞ ከደርግ ወታደራዊ መንግሥት ጋራ ቀጥሎም ከወያኔ ትግሬዎች ጋራ በፀረ ኢትዮጵያ፣ በፀረ ሸዋ ዘመቻ ላይ የተባበረ ግንባር ፈጥረዋል። የኢትዮጵያን መንግሥት ግዛት ልክ እንደ ወራሪው ፋሽስት ጣሊያን በባንቱስታን አፓርታይድ የጎሣ ክልል የሸነሸኑትና በታሪክ የሌለ፣ ያልነበረ የኦሮሚያ ክልል ተብዬ በዐማራው፤ በጉራጌውና አርጎባው ምድር ላይ ፈጥረዋል።
የአርጎባ ሕዝብ ምድርም ከዛሬው ወሎ ክፍለ ሀገር እስከ ባሌ፤ ፈጠጋር (አሩሲ)፣ ደዋሮ (ሐረርጌ) ሀርላ፣ በርበራ ዘይላ ድረስ ያለውን አካባቢ ያጠቃልል ነበር። በመሆኑም ነው ያርጎባዎች መንደር በግንብ የተሠሩት ለምሳሌ ዛሬ አሩሲ በሚባለው አርባጉጉ አውራጅ፤ በባሌ ደጋማ አውራጃ እንዲሁም በሐረርጌ ሁሉም አውራጃዎች ውስጥ በተለይም በጨርጨር፣ በወበራ፤ በጋራ ሙለታ፣ በሐረር ዙሪያ ሁሉ የአርጎባዎች መንደር ፍርስራሽና የቀጣና እርሻ ዕርከን ግንባታ ቅሪት ይገኛሉ።

**፫ኛ.** በአንድ በኩል የጋላ ዘላን ወራሪ ጎሣዎች በሉባ የደፈጣ ውጊያ ስልት በሸዋ እንዴት እንደተስፋፍና በቋሚ ሠፋሪነት መኖር እንደጀመሩ የተረከውን ሃተታ በሚፃረር ሌላው በኩል ደግሞ ከመካከለኛው ዘመን አስቀድሞ የጋላ ጎሣዎች በሸዋ ምድር ይኖሩ ነበር እያልክ ልክ ኦነግና ቀጣሪዎቹ ኦሮሚያና የኦሮሚያ ነፃ የገዳ ሪፑብሊክ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ይኖሩ የነበሩትን ከመቶ ዓመታት በፊት በዘመነ የአፍሪቃ ክፍለ አህጉር ቅርምት ወቅት በአውሮፓ ቅኝገዥዎች ርዳታና ትብብር ያበሻው የሸዋ ዐማራ አጤ ምኒሊክ ወረራ ቅኝ ተገዥ የሆነችውን አገር የብሔርን የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ነፃ ለማውጣት እየተባለ የሚነዛውን ትዕይንት ማራገብ ምን ይባላል? አስገራሚው ጉድ ደግም ጋሎች በሸዋ ነባር ነዋሪ ለመሆናቸው ግድል ጠቅሰሃል። በመጀመሪያ ደረጃ ያንዳንድ ደብተራዎች የፈጠራ ተረት ይልቁንም ገድል ተብዬው ትርኪምርኪ ለቋንቋ ጥናትና ምርምር እንጂ ለታሪክ ሰነድነት ምንም ዋጋ የላቸውም።
የኢትዮጵያ አጤዎችና ቅልብ ፀሐፊዎቻቸው ለምሳሌ ስለ ጅግናው ግራኝ አሕመድ ትውልድና ማንነት የጻፉት ፍጹም የፈጠራ ወሬ ነው። የግራኝ አሕመድ እናት የአዳል ሴት ስትሆን አባቱን ደግሞ የደብረ ሊባኖስ መነኩሴ የነበረውን ካህናቱ ደብድበው ገደሉት ብለዋል። ግራኝ አሕመድ የአዳል አርጎባ ተወላጅ ጀግና ነበር። የሚናገረውም ቋንቋ አርጎብኛና አረቢ ስለነበር የዘይላ ይማም ተብሏል። ግራኝ አሕመድን ከሱማሌ ጎሣ ወገን እንድሆነ አድርገው የሱማሌ እስላም አረብ ዘርያ ነን ባይ ኩሻዊ ጎሣዎች የፈጠራ ትርኢት በሬው ላም ወለደ ነው።
ኢትዮጵይን በጠቅላላው ለአስራ አራት ዓመታት ያህል በተለይም ሕዝበ ክርስቲያኑን ጠረኛው ግራኝ በቱርክና አረብ ርዳታ እንቀጥቅጠ ስለገዛቸው ሽንፈታቸውን ለመሸፋፈን ሲሉ ግራኝን ጭራቅ አድርገው ቢመስሉት ከቶ አያስገርምም። ቁመቱ አርባ ክንድ ነበር ብለው አሿርተዋል። በደቡብና በመሓል አገር የሚገኙትን በጣም ጥንታዊ ቁም ትክል ድንጋይ ሕውልቶችን በጅማላ ግራኝ በአንድ እጁ የተከላቸው ተብሎ ተናፍሷል። የግራኝ የጦር ልብስ በጎጃም አድባራት ውስጥ የሚገኘው ቅርስ ግን ትክክለኛውን ታሪክ ያሳያል።

በድርሳነ ራጉኤል ቃል እግዚእብሔር ግራኝን ያስነሳው አጤ ልብነ ድንግል ለመቅጣት ነው ይላል። ምክንያቱም አጤው ከክርስትና እምነት ተሳልፎ የጋላ አእዋሚ ባሕልና ሥርዓት በመከተሉ ነበር ተብሏል። ነገር ግን በዘመነ ልብነ ድንግል (1508-1540) የጋላ ባሕልና አኗኗር በኢትዩጵያ ግዛት ውስጥ ፈጽሞ አይታወቅም ነበር።

ለዚህም የፖርቱጋል መንግሥት መልክተኞች አነ ፍራንሶዋ አልቫሬስ ለስድስት ዓመታት ያህል በኢትዩጵያ ቆይተው ሲመለሱ ያዘጋጁት ዘገባ ስለ ጋሎች ምንም ማስረጃ የለም። ቫልተር ጠለዝ የተብላው ፖርቱጋላዊ የጅኦግራፊና የታሪክ ሊቅ የጋሎችን አገር ከባሌ ወዲያ ቤናድር ደቡብ ሱማሌ አካባቢ መሆኑን አመልክቷል። እንዲሁም ጀሮኒሞ ሎቦ (1595-1678) ኢየሱሳዊ ሚሲዩን ከኬኒያ ማሊንዲ በጁባ ወንዝ በኩል ወደ ኢትዩጵያ ለመግባት ተጉዞ በዚያው አካባቢ የሚኖሩትን ጋሎች አግኝቶ ጉዞው በጣም አደገኛና እንደማይቻል ነግረውት እንደተመለሰና ወደ ቀይባሕር አቅጣጪያ ተጉዞ በደንከል በኩል ኢትዩጵያ ገብቶ በአጤ ፋሲል እስኪባረር ድረስ መቆየቱ ያባይን ወንዝ መነሻ ምንጭ አስመልክቶ መጻፉ ይታወሳል።

በስፍራና በጊዜ ፈጽሞ የማይገናኙ ድርጊቶችን መወሻከት፤ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን የጋላ ወረራና ቋሚ ሠፋሪነት ወዲህ የተፈጸሙትን ኩነቶች አንዳንድ ጸሐፊዎች ከጊዜ በኋላ የፈጠሩት ተረት ተረትን የታሪክ ሰነድ አስመስሎ ይልቁንም በተከታታይ ለወቅቱ የጎሣና የባንቱስታን የዘር ፖለቲካዊ ሽንገላና ትርፍ አቶ ዳንኤል ክብረት ሲያስተጋባ ተደምጧል።

ከዚህም ሌላ ከግራኝ የ14 ዓመታትና ከተከታዩ የአረመኔ የጋላ ሉባ በየስምንት ዓመት ወረራ፤ ሰለባ፣ ዝርፊያና እልቂት በፊት የተጻፉት በያለበት ወድመዋል።

ሆኖም ግን ሳይወድሙ የተረፉት ጥቂት መጻሕፍት በጋሞ ብርብር ማርያም፤ በዟይ ሕይቅ ደሰቴዎችና በሌሎች ሰዋራ ገዳማት እንደሆነ ይታወቃል። ከ17ኛው የጎንደር መንግሥት ዘመን ወዲህ አንዳንድ ቅጅዎች ቢዘጋጁም ይዘታቸው እጅግ በጣም አጠያያቂ ነው።

የሸዋ የኢትዩጵያ መንግሥት መሥራች አጤ ይኩኖ አምላክን (1270--1285) የጋላ ውላጅ አድርጎ የቀረብው ተረት እንዲሁም በአጤ ዳዊት (1382-1411) ዘመን ተጻፈ ያለው የቀውስጦስ ተብዬ ገድል ፍጹም የቅርብ ዘመን የፈጠራ ተረት መሆኑን እንገልጻለን።

ባማርኛ እና በጋሊኛ ተመሳሳይ የሆኑ ቃላትን ይልቁንም ጋሊኛ ከዐማርኛ የወረሳቸውን ቃላት በመመልከት ብቻ የጋላ ጎሣዎች ቱላማዎች፣ ሜጭያዎችና ከረዩዎች በመሐል አገር ሸዋ ከ1665 ዓ.ም በፊት ይኖሩ እንደነበረ ዳንኤል ክብረት የሚለፍፍው የኦነግ እና ቀጣሪዎችን የፈጠራ ድርሰት ማለትም Being and becoming an Oromo በፈረንጁ ፀረ ኢትዩጵያውያን አነ ሆልኮምብ፤ ባክስተር፣ ሁልቲን፤ ማርካኪስ፤ ዳቪድሰን፤ ችሩሊ ወዘተረፈ በጎሣ፣ በሥነ ሰብ፣ በሥነ ቅርስ፤ በቋንቋ፤ በታሪክና ባሕል፤ በሃይማኖት ጥናት ሽፋን የጎሠኝነት አስፋፊ የንግድ ተቋማት (Ethnic entrepreneurs) ትርካት ከማቀንቀን ውጪ ምንም ዋጋ የለውም። ይህም የጋላ ልሂቃን እነ አሰፋ ጀለታ፤ መሐመድ ሐሰን, ሙኩሪያ ባልቻ፤ ነጋሶ ጊዳዳ፤ ሕዝቅያስ ገቢሳ፤ ፀጋዬ እራርሳ፤ ነቢዩ ገለታ፤ ታደስ ጣሓ፤ ዘገየ አሰፋ፤ ወዘተረፈ ለኦሮሚያ ሪፑብሊክ ምሥረታ የሚነዙትን የፈጠራ ትርካታ ማስተጋባት ነው።

በአቶ ዳንኤል የገድላት ትረካት እንደ ሰገሌ፣ መንዲዳ፤ ለሚ፣ ገላን፣ ወሊሶ፤ ጨንጌ፣ ጭያላ፣ ሲሬ፤ ሰኮሩ፤ ጎርፎ፣ ሠሪቴ፤ ጨፌ ወዘተረፈ የመሳሰሉት የጋልኛ ቃላት መኖር ለነባር ሕዝብነት ማረጋገጪያ ማድረግ ምን የሚባል ቅኘት ይሆን?

ባማርኛ ስርቴ በተቀዳሚ የአንስተኛ ዕፅ የቀስተንቻ መጠሪያ ነው። በሌላ በኩል ሰሪቴ ሻጠ ሲባል ሲያውቅ አበድ፤ ወፈፌ፤ እብድ ማለት ነው። ሰገል ሰገሌ ማለት አድም ጠንቋይ ሁለትም ስስታም ቀብቃባ፤ ብዙ በላተኛ ነው። ከጋልኛው ሰገሌ ድምፅ፣ ዜማ ፤ ዜና ማለት ጋራ በጭራሽ አይገናኝም። ለሚ የሚለው ያማርኛ ቃል ትርጉሙ የሚለማ፣ ለምላሚ ማለት ነው። ጎርፎ የቀበሌ ስም ከግራኝ ወረራ በኋላ አቶ ጎርፉ የተባለው የሸዋ ቱላማዎችን ወደ ግራርያ ሰላሌ አውራጃ ያስገባ ሰለሆነም ነው በስሙ ጋራ ጎርፎ የሚባለው። ጨፉ፤ ጨፌ ማለት ባማርኛ መስክ፣ ለምጨቅ፤ ጨቆ ማለት ነው። ሌላው የጨፌ ትርጉም ጠጉራም ጋቢ ቡልኮ ነው።

ነደድ፤ ነዳዲ መንድድ ወይም መናድድ ማቀጣጠያ፤ መንደጃ፤ መንደድ ተቃጣይ፤ ቦግ ቱግ ማለት ከጥንት ወረብ የሙገር ቆላ ስፍራ በሰላሌ አውራጃ ውስጥ <u>ካራ አባ ገሙ መንዲዳ</u> የተባለ የኮተሊክ ሚሲዩን ከዘመነ አጤ ምኒልክ ወዲህ ይገኝ ነበር። ደብረ ብርሃን አቅራቢያ በቅርብ ዘመን ከአንጎለላ በስተምሥራቅ ያለውም የኮተሊኮች ሠፈር መንዲዳም ስሙን በቀጥታ ያገኘው ከሰላሌው ነው። በመንዲዳ መንደር አጠገብ ሰኮሩ የሚባል ወንዝ ሆነ ኩሬ የለም። ከዚህም ሌላ በመንዲዳ መንደር አስቀድሞ የቴዎድርስ ስማዕት ቤተክርስቲያን አልነበረም። በደብረብርሃን አጠገብ ያለው መንዲዳ የሚገኘው በጥንቱ <u>ዝንጃሮ</u> ወረዳ ውስጥ ነው። ዝንጃሮም ከአጤ አምደ ጽዩን ጀምሮ ወሕኔ ቤት ነበር።

በኢትዩጵያ ታሪክ ስመ ገናናው ያጤ ይኮኖ አምላም ውላጅ አጤ ዓምደ ጽዩን ግብረ መስቀል (1314-1344) ከተጉለት መዲናው ሃድያን፣ ወጅን፣ ደዋሮን፣ ባሌን፣ ጋፋትን፣ ዳሞትን፣ አገውን፣ ይፋትን፣ ትግሬን፤ አዳልን በጦር ኃይል ያስገበረና ግዛቱን ሲያስፋፉ በዚያን ወቅት አንድም የጋላ ጎሣ አገር ስም አልተመዘገበም። የአጤ አምደ ጽዩን ሠራዊት አንኮበር ላይ ከሁሉም ግዛቶቹ ከተሰበሰበ በኋላ ወደ አዳል አገር ዘመቻ የአዋሽን ወንዝ ተሻግሮ የደዋሮን ግዛትም አልፎ በአዳል አገር እስከ ዘይላ በርበራ ድረስ ለአራት ወራት ያህል ቆይቶ አዳልን አስግብሮታል። ስለሆነም ነው ያጤ አምደጽዩን ጠረኛነት በእሲያ፤ በአውሮፓና በአፍሪቃ በሰፊው የተሰራጨው።

አጤ አምደ ጽዩን ከደብረ ሊባኖስ ተዋሕዶ መነኮሳት ጋራ በመጣላቱ ምክንያት በየአገሩ በታትኗቸዋል። አባ አናሪዎስን ወደ ባሌ ልኮታል። ዕጨጌ ፊሊጶስን ወደ

ግሼ፣ ሌሎች አያሌ መነኮሳትን ደግሞ ወደ የረር፤ ዟይ ሐይቅ፤ ጉራጌ፤ ከምባታ፤ ጋሞ፤ አሰቦት እንዲሁም ወደ ትግሬ እና ደምቢያ፤ ወደ በጌምድር ሰሜን ዋልድባ፤ ጎጃም ጣና ሐይቅ፤ የተላኩ እንደሆነ ይታወቃል። አባ ፍሊጶስ ነው በሐማሴን የደብረ ቢዘንን ገዳም በአጼ ዳዊት (1382-1411) ርዳታና ድጋፍ የመሠረተው። አጤ ዳዊት የተወለዱት በሸዋ የእንደግብጣን አካባቢ በወረብ ወይም

መናገሻ አውራጃ ውስጥ ነው። ዋና መዲናቸውም በዚሁ ሥፍራ ከየረር በሰተምዕራብ፤ ከእንጦጦ በሰተደቡብ፤ ከዝቋላ ተራራ በስተሰሜን፣ ከበስተምዕራብ ከወጨጭያና ከመናገሻ ተራሮች በእንዶጥና ወይም በረራ ነበር። የአጤ ልብነ ድንግል ያጤ ሚናስ ዋና ሰፈር እንጦጦ ላይ ነበር።

አጤ ዳዊት በጣም ሃይማኖተኛ ስለነበሩ አቃቤ ሰዓት የነበሩት የሐይቅ እስጢፋኖስ መነኮሳት በፈጠሩባቸው ሴራ ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው ለልጃቸው ለቴዎድሮስ ለቀው ጥቂት ቆይተው ሞተዋል። ቴዎድሮስም ሦስት ዓመት ብቻ ገዝቶ ስለሞተ መራቤቴ አውራጃ ውስጥ ተቀብሯል።

ቀጥሎም አጤ ይስሐቅ (1414-1429) ነግሦ የኢትየጵያን ግዛት አስፋፍቷል፤ አዳልን ዛይላና በርበራ ድረስ በመዝመት አስግብሯል። በደቡብና በምዕራብ ኢትዮጵያ ባር ጋሞ፤ ሱጋሞ፤ እናሪያ ጎንጋ፣ ከፋ ጋምቤላ ድረሰ ያለውን አገር ግዛቱ አድርጓል።

በተስቦ ወረርሽን ምክንያት ከአጤ ይስሐቅ ዕረፍት በኃላ የነገሡት በተከታታይ ስለሞቱ ያጤ ዳዊት አራተኛው ልጅ አጤ ዘርዓ ያዕቆብ ቆስጠንጢኖስ (1434 1468) እጅግ በጣም የሥነ መለኮት ጠቢብ፤ ደራሲ ሊቅ እንዲሁም ጦረኛው ነገሠዋል። አጤ ዘርዓ ያዕቆብ ያደጉት አምባ ግሸን ቢሆንም የተወለዱት በእንደግብጣን ጥለቅ በምትባለው በመናገሻ ተራራ አጠገብ ነው። የለባሾ በተባለው የትውልድ አገሩ ታላቅ መካነ ዕፀዋት ያትክልት ቦታ ልዩ ልዩ የጥድ፣ የዝግባ ዛፎች የወይንና የቅመማቅመም ተክሎች ተዘጋጅተው ነበር። አጤ ዘርዓያዕቆብ ያስተከሉት ደንና ዛፎች ዛሬም በመናገሻ ተራራና ዙሪያ ይገኛሉ። ከትውልድ አገራቸው ከለባሾ መናገሻ ተነስተው በስተሰሜን አቅጣጪያ በመጓዝ የደረሱበት አካባቢ <u>ክልአት</u> ይባላል። በዚህም ለጥቂት ጊዜያት ከቆዩ በኋላ ወራሪ የተባለውን ወንዝ በመሻገር ምደረ ኤባ ደርሰዋል። ቦታውም በጣም ደስ ስላላቸው ቆዩበት።

በመሐሉም በመስቀልና በማርያም አናምንም የሚሉት ደቂቀ እስጢፋኖስ የተባሉት ሐርጣቃች በጉባኤ ክርክር ተደርጎ እንዲያምኖ ቢነገራቸውም አሻፈርን ስላሉ የካቲት ሁለት ቀን ተወገሩ።

በመጋቢት 10 ቀን በመስቀለ ክርስቶስ ዕለት ብርሃን ለሰወሰት ቀናት ያህል ስለታዩበት፤ በቦታው ላይ ወዲያው ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራ አጤ ዘርዓ ያዕቆብ አዘዙ። የቦታውን ስም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ደብረ ብርሃን ተብሎ ተሰየመ። የሸዋን፣ የግድምን፤ የይፋትን፤ የተጉለትን፣ የፈጠጋርን ጨዋዎች በማዘዝ ታላቅ ቤተ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን አሠርተዋል። የወርቅ ቅብ ጉልላት፣ የቅጥር አጥሩ ንጣት በሩቅ ያብረቀርቅ እንደነበረ በዜና መዋዕሉ በሰፊው ተመዝግቧል።

የቀድሞው ምድረ ኤባ ማላት ዝንጀሮ፤ የዝንገሮ ጨኸት፤ የዝንጀሮ መጮኺያ ማለት እንደነበር ከደብረ ብርሃን በታች አቦ ገዳም ሸለቆ ውስጥ የሚገኘው የዝንጀሮ መንጋ አፋፉን አልፎ በሜዳው ላይ ሲርመሰመስና ሲንጪያጭያ የሚያዩትን የተጉለት እረኞችና ልጆች ኤባ ገደል ገባ ይሉታል። በኢትዮጵያ ታሪክ ታላቁ አጤ ዘርዓ ያዕቆብ በደብረ ብርሃን ለ፲፱ ዓመታት ያህል ኖረዋል። አያሌ መጻሕፍትን ራሳቸው ደርሰዋል፤ በዙ የክርስትና መጽሐትንም ወደ ግእዝ አስተርጉመዋል። በዓለ ንግሣቸውንም በጥንታዊቷ አክሱም ከተማችን ወርደው ፈጽመዋል። በሐይቅ የደብረ ነጎድጋድ ገዳምን በከፍተኛ ደረጃ ሲያስፋፉ በሸዋ የዕጨጌዎች መኖሪያ የሆነውን ታላቁን የደብረ አሰቦ ገዳምን ደብረ ሊባኖስ ብሎወ ሰይመውታል። ያጤ ዘርዓያቆብ ስምና ዝና በመላው የኢትዮጵያ ከደቡብ አስከ ሰሜን፣ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ በሚገኙት ሁሉም ነገዶቼ ዘንድ ትውስታው ከትውልድ ትውልድ ታትሞ ዟልቋል።

ከአጤ አምደ ጽዩን ጀምሮ የጸሐፊ ትዕዛዝ ሹመት ተዋቅሮ ዜና መዋዕል፣ ሥርዓተ መንግሥት፤ ፍትሕ ነገሥት እና ልዩ ልዩ ሃይማኖታዊና ታሪ9ካዊ መጽሕፍት ተዘጋጅተዋል።

እስከ አጤ ልብነ ደንግል ዘመነ መንግሥት ድረስ አንድም የጋላ ነገድ ስምና ስፍራ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ አልተመዘገበም። የጋላ ነገድ ከባሌ ማዶ ኬኒያ ጠረፍ ከደቡብ ሱማሌ ቤናድር ተነስቶ የኢትዮጵያ ግዛት ባሌን መውረር የጀመረው እ.አ.አ ከ1537ዓ.ም የግራኝ አሕመድን ጅሃዳዊ ወረራን ተከትሎ ነው። አጤ ገላውዴዎስ የግራኝን ጦር ድባቅ ሲመታው የአዳል ሠራዊት ብትንትኑ ወጥቶ ፈርትጧል። ከዚህም በኋላ ነው አጤ ገላውዴዎስ ከወራሪው የጋላ ሉባ የደፈጣ ተዋጊ ጦር ጋራ ጦርነት በደዋሮና በባሌ፤ በፈጠጋር ያደረገው። ይህም ሁኔታ በኢትዮጵያ በጊዜው በነበሩት ፖርቱጋላውያን እነ ቤርሙደዝ ያይን ምስክርነት በስፍራና በጊዜ የተረጋገጠ ነው። አጤ ሚናስም ሆነ ልጁ ሠርፀ ድንግል በዘመናቸው የጋለን ወረራ ለመከላከል ያላቋረጠ ዘመቻ በሁሉም አቅጣጪያ አድርገዋል። ሆኖም ግን ከ1665 ዓ.ም ወዲህ የጋላ ቱላሚ፤ ሜጪያና ከረዩ ጎሣዎች የአዋሽን ወንዝ ተሻግረው በሸዋ ያማራ፤ የጉራጌ፣ የአርጎባና የጋፋት፤ የዳሞት ምድር ላይ በቋሚነት ሠፍረዋል። ከፊሎቹም ከሸዋም አልፈው ወደ ዳሞት፤ ቢዛሞ፣ እናሪያ፣ ጎንጋ በመስፋፋት በነባሩ ሕዝብ ባማራው፣ በጋፋቱ፤ በጋሞው፤ በወላሞው፤ በሸናሻው፣ በጋምቤላው፤ በጎንጋው፣ በከፋው፣ በየሙ፤ በአናሪያው፤ በሃድያው፤በከምባታው፤ በሲዳማው፤ ወዘተረፈ ምድር ላይ ተንሰራፍተዋል። በወረራ መጥተው የሠፈሩበትንም አገር ስም ቀይረው በየጎሣቸው ስም ሰይመዋል። ከደዋሮ (ሐረርጌ) ወደ ቤተ ዐማራ የገቡት የባሬንቱ ጋላ ነገድ አገሩን ሠሎ ብለው ከሰየሙ በኋላ የጥንት ያማራ መጠሪያ የቀበሌ ስሞችን በጎሣቸው ቅይረውታል።

የሸዋ ነባር ያማራ፤ ያርጎባና የጉራጌ ሕዝብ ለጋላ ወረራ በማያመቹት አምባዎችና ቆላማ ስፍራዎች መሸጎ እራሱን በመከላከሉ ነው ጥንታዊ ያማርኛ መጠሪያ ስሞች፤ ለምሳሌ፣ ተጉለት፣ ምንጃር፣ መራቤቴ፣ ደራ ኮራ፤ ግንደበረት፤ ሙገር፤ ዝቋላ፤ የረር፤ ሞረት፤ ጠራ፤ ገሊላ፣ ሰቃ፤ አሳግርት፤ ፈንታሌ፤ ወግዳ፤ ይፋት፣ መንዝና ግሼ፣ ግድም፣ ኤፍራታ፤ ሲና፣ ባሶ፣ አታክልት፤ ቆራሬ፣ ዲቢ፣ ሚጣቅ፣ ሰለልኩላ፤ አስቀሌና፤ አስቲት፤ አጡራ፤ ላይ ሙጠር፤ ታች ሙጠር፤ አጥላሳ፤ ጎላ፤ ዝገኔ አገር፤ ጋቺና፤ አክላስ አገር፤ አልዩ አምባ፤ ራሳ፣ አዋዲ፣ ወሲል፤ ጌታ ገደል፣ መተህ ብላ፣ ሙገሬ ዛላ፤ ሽንኮራ፤ ገረመሚ፤ ሰርማሚ፣ ወንጂ፤ ቅምብቢት ወዘተረፈ ሳይቀየሩ የዘለቁት።

እስከ ቅርብ ጊዜ ደረስ ከሸዋ ክፍለ ሀገር ፲፩ አውራጃዎች አንዱ የተጉለትና ቡልጋ አውራጃ ወረዳ አንዱ የደበረብ ብርሃን ከተማን ጨምሮ ባሶ <u>አታክልት</u> ከጥንቱ መጠሪያ በዘመነ አጤ ዘርዓ ያዕቆብ <u>ክልአት</u> ከተባለው ቃል በቀጥታ የወረደ ነው። ......... ይቀጥላል

**የጋላ ወረራና የሉባ አረመኔ የሰለባና ዝርፊያ ጦርነት ከኬኒያ እስከ ኢትዮጵያ ከታቢ ገሞራው ማንያዘዋል** TOMY.gemora16@gmail.com